# 2ኛ ትምህርት

*መስከረም 21-27 2009 ዓ.ም* *Oct 1-7*

## ታላቁ ተጋድሎ

**ሰንበት ከሰዓት**

ለዚህ ሳምንት ትምህርት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡- ኢዮብ 1፡1-5፣ ኢዮብ 1፡6 -12፣ ዘካ. 3፡2፤ ማቴ. 4፡1፣ ሕዝ.28፡12-16፣ ሮሜ 3፡26፤ ዕብ. 2፡14

መታሰቢያ ጥቅስ፡- እግዚአብሔርም ሰይጣንን፡ ሰይጣን ሆይ፥ እግዚአብሔር ይገሥጽህ፤ ኢየሩሳሌምን የመረጠ እግዚአብሔር ይገሥጽህ፤ በውኑ ይህ ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ አይደለምን? አለው። (ዘካ. 3፡2)

በመላው የመጽሀፍ ቅዱስ ገጾች (በብሉይ ኪዳን) እና (በአዲስ ኪዳን) በእግዚብሄርና በሰይጣን፣ በመልካምና በክፉ፣ በዓለምቀፋዊና በግለሰብ ደረጃ ስላለው ጠንካራ ፍልሚያ በብዙ ተዘግቦና ተጠቅሶ ይገኛል። እነዚህን ገጾች ስናነፃጽር በግለሰብ ደረጃ ያገኙት መረዳትና ምልከታ ተደምሮና ተገጣጥሞ የፈጠረውን እውነት ሰናገጣጥም አጠቃላይ የመጽሀፍ ቅዱስን መልእክት በግልጽ እንድናስተውል ያደርገናል።›› The Handbook of Seventh-day Adventist Theology, p. 969

የታላቁ ተጋድሎ ፍሬ ሀሳብ የመጽሀፍ ቅዱስን ‹‹አጠቃላይ መልእክት›› በተለይም የድነትን እቅድ በላቀ ደረጃ ማስተዋል እንድንችል ምልከታን ይሠጠናል። ምንም እንኳን በአዲስ ኪዳን ላይ ይህ አብይ ሀሳብ በጉልህ ተንፀባርቆ ቢታይም በብሉይ ኪዳን ላይም ተገልጾ ተቀምጦልናል። ምናልባትም እንደ ኢዮብ መጽሐፍ በግልጽ ስለሰይጣንና ተጋድሎው ፍንትው አድርጎ የገለጸ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ የለም።
በዚህ ሳምንት ፊት ለፊት ተገልጾ ከተቀመጠልን እውነት በሰተጀርባ ያለውን የኢዮብ ዋነኛ ትኩረት ያረፈበትን ሰፊውን አውነታ እንቃኛለን። ምንም ያህል ህይወታችንና ታሪካችን ከኢዮብ ታሪክ የተለየ

ቢሆንም ከእርሱ ጋር የምንጋራው አንድ ነገር ግን አለ፤ ልክ እንደ ኢዮብ እኛም በተጋድሎው ውስጥ የተካተትን የተጋድሎው ተሳታፊዎች ነን።

**የዚህን ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለመስከረም 28 ሰንበት ይዘጋጁ።**

*እሁድ መስከረም 22* *Oct 2*

## በምድር ላይ ያለች ትንሽ ሰማይ በምድር ላይ ያለች ትንሽ ሰማይ

የኢዮብ መጽሀፍ በአንጻራዊነት ስናየው አጀማመሩ አዎንታዊ ነው፤ ቢያንስ በዓለማዊ እይታ ብናይ በሁሉም ረገድ ተባርኮ ያለን ሰው እናገኛለን።
**ኢዮብ 1፡1-4ን አንብቡ። ጥቅሱ ኢዮብ ምን አይነት ህይወት ይኖር እንደነበር ምን ይገልጽልናል? የኢዮብ መኖር በጎ ተጽእኖ ምን ነበር?**

---

---

---

ኢዮብ በእርግጥም የጽድቅ ባህሪን ጨምሮ ሁሉም ነገር የነበረው ሰው ነበር። ኢዮብ 1፡1 ላይ ‹‹ነቀፋ የሌለበት›› ተብሎ የተተረጎመው ቃል "ሙሉ" ወይም "በቅንነት የተሞላ" የሚል ትርጉም ካለው ቃል የመነጨ ነው። "ቅን" የሚለው ቃል "ቀጥተኛ" ማለት ሲሆን ቀጥ ባለመንገድ መራመድ የሚል አንድምታ ያለው ነው። በአጭሩ መጽሐፉ በታማኝነትና በቅንነት የሚሄድን ሁሉም ነገር ያለውን ባለጸጋ እያሳየ የኤደን ገነትን ያህል በተዋበ አጀማመር ይጀምራል። በዚህ በወደቀ አለም ወስጥ ሆኖ ግን ሁሉም ነገር ነበረው።
**ኢዮብ 1፡5-6ን ያንብቡ። ይህ ክፍል ኢዮብ ይኖር በነበረ ጊዜ ስለነበረው የወደቀው አለም እውነታ ምን ይነግረናል?**

---

"በወንድና ሴት ልጆቹ የጨዋታ ጊዜ መካከል ልጆቹ እግዚአብሔርን አሳዝነው ይሆናል ብሎ ያስባል።

ለቤተሰቡ ታማኝ ካህን እንደመሆኑ መጠን ለእያንዳንዳቸው መስዋዕትን ያቀርብላቸዋል። የኃጢአትን አስከፊነት ያውቃል፤ ልጆቹም ምናልባት የመለኮትን መንገድ ዘንግተው እንደሆነ ብሎም ያስባል። በእነርሱ ምትክ ሆኖም ሊማልድላቸው ይቀርባል" -Ellen G. White Comments, The SDA Bible Commentary, vol. 3, p. 1140

በጉልህ እንደምናየው እስከዚህ ድረስ ኢዮብ በመልካም ሁኔታ ተደላድሎ ያለ ሰው ነበር። በኤደን ገነት ታሪክ እንደነበረው መልካም አጀማመር ሁሉ የተሟላ ህይወት ያለውና ትልቅ ቤተሰብ የነበረው ስመጥር እና ብዙ ንብረቶች ያሉት ሰው ነበር። ያም ቢሆን ግን ይህ ኑሮ እየተኖረ ያለው በኃጢያት ወድቃ ባለች ፕላኔት ውስጥ ነበር። ኢዮብ በዚህ መኖር የሚያመጣውን አደጋ በቅርቡ ሊያይ ነው።

**በአሁኑ ሰዓት በህይወትዎ መልካም የሆነ ነገር ምንድነው? ስለነዚህ መልካም ነገሮች ሁልጊዜ የአመስጋኝነት አመለካከት ሊኖረን የሚችለው እንዴት ነው?**

*ሰኞ* *መስከረም 23* *Oct 3*

## ዓለምቀፋዊ ግጭት

የኢዮብ መጽሀፍ በምድር ላይ ፀጥታና ሰላም ሰፍኖ ስለነበረበት ቦታ በማውሳት ይጀምራል። ሆኖም ግን በመጀመሪያው ምዕራፍ ቁጥር 6 ላይ ታሪኩ ወደ ሌላ ቦታ ይወስደናል። ወዲያውኑ በመለኮት መገለጥ ኃይል ካልሆነ በቀር በሰብአዊ አይን ሊታይ ወደማይችል ልዩ ስፍራ ይወስደናል። በጣም የሚገርመው ደግሞ ይህ ልዩ የሆነው ስፍራ ማለትም ሰማይ ቢያንስ በመጀመሪያ ሲታይ እንደ መሬት ፀጥ ያለና ሰላማዊ የነበረ አይመስልም።

**ኢዮብ 1፡6- ኢዮብ 1፡6-12ን ያንብቡ። ይህንን ክፍል በዚህ ሩብ አመት የበለጠ በዝርዝር ቆይተን የምናጠናው ቢሆንም በዚህ ስፍራ ላይ እየተከናወነ ያለው ነገር ምንድነው? በምድር ላይ ኢዮብ እየሆነለት ካለው ነገር ጋር እንዴት ይቃረናል?**

በዚህ አጭር ክፍል ውስጥ ብዙ መርምረን የምናወጣቸው ነገሮች አሉ። ሕዋን የሚያሳዩ ቴሌስኮፖች የማይደርሱበትን እንዲሁም ሳይንስ ያልደረሰበትን የዩኒቨርስን ገጽታ የሚገልፁ ቁጥሮች ናቸው። አስደናቂው ነገር ግን ዓለምቀፋዊውን ግጭት ፍንትው አድርገው ማሳየታቸው ነው። በዚህ ክፍል ላይ የምናገኘው የተረጋጋ፤ ሰላማዊ እና ፀጥ ያለ ንግግርን አይደለም። እግዚአብሔር ስለ ኢዮብ (በሰውኛ አገላለፅ) ልክ አባት በልጁ ኩራት ተሰምቶት እንደሚናገር ተናገረ። በታቃራኒው ሰይጣን እግዚአብሔር ስለኢዮብ በተናገረው ነገር ላይ በማሾፍ ተናገረ “ሰይጣንም ለእግዚአብሔር እንዲህ ብሎ መለሰለት፦ በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራው በከንቱ ነውን?” (ኢዮብ 1:9) ማሽሟጠጥ በሚመስል ቅላጼ ይመስላል ሰይጣን እግዚአብሔርን በማንኳሰስ የተናገረው።

ጥቅሱ በግልጽ ይህ ክርክር የተከናወነው በሰማይ ነው ብሎ ባይናገርም በእርግጠኝነት እዚያ ነበር ብለን መናገር እንችላለን። የሆነው ግን አንድ ፍጡር የሆነው መልአክ ፊት ለፊት ሊገዳደረው በእግዚአብሔር ፊትና ‹‹በእግዚአብሔር ልጆች›› ፊት ቆመ። ለምድራዊ መሪዎች እንኳን አንድ ሰው በእንዲህ መልኩ ሲናገር መገመት ያዳግታል። ይህ ግን አንድ ፍጡር በእግዚአብሔር በራሱ ላይ ያደረገው ነው። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

የዚህ ምላሽ በተለያየ መልኩና በተለያየ ስፍራ ባሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ይገኛል። ይህም ታላቁ ተጋድሎ ይባላል። ይህም ስለ ኢዮብ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተገለጸው የኃጢያት ታሪክ እና በምድር ስላለው ስቃይ ያትታል። ከዚህ በላቀ ደግሞ የሱስ በኃጢአት ምክንያት የመጣብንን ችግር እና የምድርን ስቃይ ለማስወገድ በመስቀል ላይ ስለፈጸመልን ነገር የበለጠ እንድንረዳ ያደርገናል።

*ማክሰኞ መስከረም 24* *Oct 4*

## ግጭት በምድር ላይ

የኢዮብ መጽሐፍ መጋረጃውን ከፍቶ አይኖቻችንና ጆሮዎቻችን ያልተረዱትንና አለማዊ ፍልስፍና ፈጽሞ ሊያሳየን የማይችለውን እውነት ገላልጦ ያሳየናል። (ትልቁን ምስል ለማየት አይኖቻችን፤ ጆሮዎቻችንና

አለማዊ ፍልስፍናዎች ውስን ስለመሆናቸው ይህ ክፍል ያመለክተናል) እነዚህ ጥቅሶች በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ስላለው ተጋድሎ ያሳዩናል። ምንም እንኳን በኢዮብ መጽሐፍ ላይ የምናገኘው ተጋድሎ የተጀመረው በሰማይ ቢሆንም ወዲያውኑ የተጋድሎው ስፍራ ወደ ምድር ወርዶ ይታያል። በመላው የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ እየተከናወነ ስላለው ውጊያ የሚገልፁ ጥቅሶች አሉ። ይህ ተጋድሎ ደግሞ እኛንም ያካተተ ነው።

**የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ። በምድር ላይ ካሉት የክፉ መንፈስ ኃይላት ጋር ስለሚካሄው ጦርነት እውነታነት ምን ይነግረናል? ስለሚካሄው ጦርነት እውነታነት ምን ይነግረናል?**

ዘፍ. 3:1-4

---

ዘካ. 3:2

---

ማቴ. 4:1

---

1ኛጴጥ. 5:8

---

1ኛዮሐ. 3:8

---

ራዕይ 12:9

---

እነዚህ ጥቅሶች እጅግ ለቁጥር ከሚታክቱ ጥቅሶች መካከል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኃያሉ ፍጡር ሰይጣን ስለመኖሩና ስለተንኮል ሀሳቡ በጥቂቱ የሚዳስሱ ናቸው። አንዳንዶች ሰለሰይጣን የሚነገረው ነገር ጥንታዊ አፈ-ታሪክ እንደሆነ አድርገው ቢያስቡም እኛ ግን ግልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ስላለን በዚህ ማታለያ ተጠልፈን ልንወቅድ አይገባም።

አሁን እንኳን በአለማችን ላይ ሰይጣን እያደረገ ያለውን ተግባር እውነታነት የምንረዳው በምን መንገድ ነው? የኛ ብቸኛ መሸሸጊያ ታዲያ ምንድነው? የምንረዳው በምን መንገድ ነው? የኛ ብቸኛ መሸሸጊያ ታዲያ ምንድነው?

የኢዮብ መጽሐፍ የመክፈቻ ትዕይንቶች ጥቂት ወሳኝ ነጥቦችን ያስቀኙናል፡፡ በቅድሚያ እንደገለጽነው አሁን ከምናውቀው በላቀ ሁኔታ ያለውን ሰማያዊ እውነታ ማለትም ከእግዚአብሔር ውጪ በሰማይ ስላሉ ፍጡራን ያሳየናል፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ምድራዊ ህይወታችን ከሰማያዊው ግዛት ጋር ምን ያህል የተሳሰረ መሆኑን በግልጽ ያመለክተናል፡፡ በምድር ላይ የሚከናወኑ ድርጊቶች ሁሉ በሰማይ ካለው ህይወት ተቆርጦ የተለየ አይደለም ፡፡ሦስተኛ ልክ በምድር ላይ እንዳለው ሁኔታ ሁሉ በሰማይ ስላለው የግብረ-ገብ ግጭት ያሳየናል፡፡ በአጭሩ እነዚህ የመክፈቻ ጥቅሶች ቀጥሎ ያሉትን ሀሳቦችና ታላቁ ተጋድሎን በመጠኑ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ጥቅሶቹ የሚነግሩን በአለም አቀፍ ደረጃ ያለው ታላቁ ተጋድሎ አንዴት በአንድ ግለሰብ፣ በኢዮብ ህይወት ተገልጦ እንደታየ ነው፡፡ እንደምንመለከተውም የሚዳሰሱት ጉዳዮች እኛንም ያካትታሉ፡፡ የኢዮብ መጽሀፍ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር የተጋፈጠበትን ሁኔታ ያሳየናል፡፡ ያልነገረን ነገር ይህ እንዴት እንደተጀመረ ብቻ ነው፡፡ የሚከተሉት ጥቅሶች ስለተጋድሎው የተሻለ መረዳት እንዲኖረን የሚያደርጉት እንዴት ነው? ኢሳ. 14፡12 -14፣ ህዝ.28፡12-16፣ 1ኛጢሞ.3፤6

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

*ረቡዕ መስከረም 25* *Oct 5*

## ኢዮብ እንደ ትንሽ አለም ኢዮብ እንደ ትንሽ አለም

የኢዮብ መጽሐፍ የመክፈቻ ትዕይንቶች ጥቂት ወሳኝ ነጥቦችን ያስቀኙናል፡፡ በቅድሚያ እንደገለጽነው አሁን ከምናውቀው በላቀ ሁኔታ ያለውን ሰማያዊ እውነታ ማለትም ከእግዚአብሔር ውጪ በሰማይ ስላሉ ፍጡራን

ያሳየናል። ሁለተኛ ደግሞ ምድራዊ ህይወታችን ከሰማያዊው ግዛት ጋር ምን ያህል የተሳሰረ መሆኑን በግልጽ ያመለክተናል። በምድር ላይ የሚከናወኑ ድርጊቶች ሁሉ በሰማይ ካለው ህይወት ተቆርጦ የተለየ አይደለም ።ሦስተኛ ልክ በምድር ላይ እንዳለው ሁኔታ ሁሉ በሰማይ ስላለው የግብረ-ገብ ግጭት ያሳየናል፡ ፡ በአጭሩ እነዚህ የመክፈቻ ጥቅሶች ቀጥሎ ያሉትን ሀሳቦችና ታላቁ ተጋድሎን በመጠኑ የሚያሳዩ ናቸው፡ ፡ ጥቅሶቹ የሚነግሩን በአለም አቀፍ ደረጃ ያለው ታላቁ ተጋድሎ አንዴት በአንድ ግለሰብ፣ በኢዮብ ህይወት ተገልጦ እንደታየ ነው። እንደምንመለከተውም የሚዳሰሱት ጉዳዮች እኛንም ያካትታሉ። የኢዮብ መጽሀፍ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር የተጋፈጠበትን ሁኔታ ያሳየናል። ያልነገረን ነገር ይህ እንዴት እንደተጀመረ ብቻ ነው። የሚከተሉት ጥቅሶች ስለተጋድሎው የተሻለ መረዳት እንዲኖረን የሚያደርጉት እንዴት ነው? ኢሳ. 14፡12 -14፣ ህዝ.28፡12-16፣ 1ኛጢሞ.3፤6

---

---

ኤለን ጂ. ኋይት ‹‹የፍቅር ህግ›› የእግዚአብሄር መንግስት መሰረት እንደሆነ ትናገራለች። እግዚአብሔር ‹‹በማስገደድ የሚሆን መታዘዝ›› ስለማይፈልግ እርሱ ለሰብአዊ ፍጥረት ሁሉ ‹‹የመምረጥ ሙሉ ነጻነትን›› ሰጠ። ቢሆንም ግን ‹‹እግዚአብሔር ለፍጥረታቱ የሰጠውን ነጻነት የሚያጣምም አንድ ፍጡር አለ። የኃጢያት መነሻ የሆነው እራሱ ከክርስቶስ ቀጥሎ የነበረውና በሰማያዊ ስፍራ በሚኖሩ ፍጥረታት መካከል ክቡርና ኃያል በእግዚአብሄርም የተከበረውነበር።›› Patriarchs and Prophets, pp. 34-35 ኤለን ጂ. ኋይት ከዚያም በኢሳያስና በህዝቅኤል የተነገረውን ክፍል በመጥቀስ ስለ ሰይጣን አወዳደቅ ገልፃለች።

እዚህ ጋ ያለው ዋንኛ ሀሳብ ‹‹የፍቅር ህግ›› እና የምርጫ ነጻነት እውነታ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን እንደሚነግረን ሰይጣን በውበቱና በክብሩ ተመክቶ ራሱን ከፍከፍ አደረገ። ይህ ለምን ሊሆን እንደቻለ አናውቅም። 2ኛ ተሰ.2፡7 ላይ ‹‹የአመፅ ሚስጥር›› ብሎ የተገለጸው ኃሳብ መሆን አለበት። የእግዚአብሔር ህግ የመንግስቱ መሰረት የመሆኑን ጥብቅ ትስስር ስንረዳ ሙሉ መልዕክት ይሰጠናል። ዋናው ኃሳብ ሰይጣን በኢዮብ መጽሐፍ የተገለፀበት ወቅት ውድቀቱ ካለፈ በኋላ ነው፤ የተጀመረው ተጋድሎም ቀጥሏል፡ ፡

**በአሁን ሰአት ለምርጫ የተቸገራችሁባቸው ወሳኝ ጉዳዮች ምንድናቸው? ትክክለኛውን ምርጫ ስለመምረጣችሁ ማረጋገጫ የሚሰጡ የመጽሀፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች የትኞቹ ናቸው?**

## መልሶች፡-በመስቀል ላይ

የኢዮብ መጽሀፍ በጣም ጠቃሚ ጉዳዮችን የያዘ ክፍል ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጉዳዮች ሁሉ በቂ ምላሽ በዚሁ መጽሐፍ ያገኛሉ ማለት አይደለም፡፡ ሌሎች የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍሎች የግድ ያስፈልጉናል፡፡ ያም ቢሆን ‹‹አሁን የምናየው በመስታወት ውስጥ እንደሚታይ በድንግዝግዝ ነው፡፡›› (1ኛ ቆሮ. 13፡12)

ለምሳሌ ትላንት እንደተመለከትነው በኢዮብ መጽሐፍ ስለሰይጣን አመጽ አነሳስ የሚነግረን አንዳችም ነገር የለም፡፡ ሰይጣን በስተ-መጨረሻ በታላቅ ተጋድሎ ፍልሚያ እንዴት እንደሚሸነፍም አያትትም ፡፡ እውነታው በመጽሐፍ ውስጥ በዋነኝነት እርሱን የምናገኘው በሁለት ክፍል ላይ ብቻ ነው፡፡ (ኢዮብ 1፡6-12፣ ኢዮብ 2፡1-7) ከዛ በኋላ ሰይጣን ድጋሚ ወደ ትእይንቱ ሲመጣ አይታይም፡፡ እርሱ ያመጣው ጥፋት የቆየ ቢሆንም እርሱ ግን ከዚያ ስፍራ ጠፍቷል፡፡ የቀሩት የመጽሀፍ ክፍሎችም ሰይጣንን ሲጠቅሱ አይታይም፡፡ በዚህ ፈንታ በእያንዳንዱ ክፍል ላይ ስለእግዚአብሔር በብዛት ተጠቅሷል፡፡ ይህ ደግሞ የበለጠ ትርጉም ይሰጣል፡፡ ምክንያቱም በስተ-መጨረሻ የኢዮብ መጽሐፍ ስለ እግዚአብሄርና እርሱ በትክክል ማን እንደሆነ በመናገር ስለሚደመደም ነው፡፡

ቢሆንም ግን መጽሀፍ ቅዱሳችን በታላቅ ተጋድሎ ውስጥ ስለ ሳይጣን መሸነፍ ላለን ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጠን አያልፍም፡፡ የዚህ ሽንፈት ዋነኛ ማዕከል ደግሞ የየሱስ በመስቀል ላይ መሞት ነው፡፡

**የሚከተሉት ጥቅሶች የሱስ ያደረገው ነገር ታላቁን ተጋድሎ ወደ ፍጻሜ እንዴት እንደሚያመጣ ምን ይነግረናል? ዮሐ. 12፡31- እንደሚያመጣ ምን ይነግረናል? ዮሐ. 12፡31-32፣ ራዕይ 12፡10 ፣ ራዕይ 12፡10-12፣ ሮሜ 3፡26፣ 12፣ ሮሜ 3፡26፣ ዕብ.2፡14**

---

---

በመስቀል ላይ ሰይጣን ሙሉ በሙሉ ነፍሰ-ገዳይ ስለመሆኑ ለዩኒቨርስ ሁሉ ተጋልጦ ታየ፡፡ በሰማይ ነግሶ የተመለከቱት የሱስ በሰይጣን ወጥመድ ወድቆ ተዋርዶ መመልከታቸው አስደነቃቸው ያ ደግሞ የሱስ

በዮሐንስ 12 ላይ የተነጋገረው በሰይጣን ላይ ያለ ‹‹ፍርድ›› ነው፡፡ በመስቀሉ አዳኙ ለአለም ሀጢያት ሁሉ ሲሞት (1ኛ ዮሐ. 2፡2) ያኔ ብቻ ሰማይ ድነት አሁን መጥቷል ብሎ ማወጅ ይችላል፡፡ አለም ከመፈጠሩ በፊት የተሰጠ መለኮታዊ ቃል ኪዳን እነሆ (2ኛጢሞ. 1፡9) እውን ሆነ፡፡ በእኛ ምትክ ስለሞተ ‹‹እርሱ ራሱ ጻድቅ ሆኖ በየሱስ የሚያምነውን የሚያፀድቅ መሆኑን ለማሳየት ነው›› (ሮሜ 3፡26)፡፡ ይህ ማለት በመስቀሉ አማካኝነት

እግዚአብሔር ህጉን ሳይሽር (ፃድቅ ሆኖ) ህጉን የጣሱትን ማዳን አይችልም ያለውን ክስ ውድቅ አደረገበት፡፡ ከቀራኒዮ በኋላ የሰይጣን ሽንፈት ተረጋገጠ፡፡

**በታላቁ ተጋድሎ ሆነን እየገጠሙን ባሉ ችግሮች ውስጥ እየኖርን እንኳን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለኛ ስላደረገው ነገር በማሰብ መደሰትን የምንለማመደው እንዴት ነው?**

*አርብ መስከረም 27* *Oct 7*

## *ተጨማሪ ሀሳብ*

በመልካምና በክፉ መካከል ስላለው ተጋድሎ የሚናገረው ፅንሰ-ኃሳብ በብዙ ባህሎች ዘንድ ይገኛል፡፡ በሺህ አመታት ውስጥ ይህ የተጋድሎ ሀሳብ በብዙ አፈ-ታሪኮች (ተረቶች) ላይ ተጠቅሷል፡፡ ዛሬ በከፍተኛ ትችትና የዘመናዊነት ተጽእኖ የተነሳ አያሌ ክርስቲያኖች የሰይጣን እና የክፉ መላእክትን እውነታነት ክደዋል፡፡ የተለያዩ ክርክሮችም እየተስተናገዱ ነው፡፡ እንደ አድቬንቲስትነታችን ስለ ሳይጣንና መላእክቱ የተገለጸውን አውጥተን መጽሀፍ ቅዱስን ማስተዋል እንደማንችል እንረዳለን፡፡

ሁሉም ክርስትያኖች በመልካምና በክፉ መካከል እየተካሄደ ያለውን አለምቀፋዊ ግጭት እውነታነት ክደው አልወደቁም፡፡ ለምሳሌ ግሪጎሪ ቦይድ የተባለ የወንጌላውያን (ኢቫንጂሊካል) ሊቅ ዘመን ጠገብ ስለሆነው (ዘላለማዊ ግን ስላልሆነ) የእግዚአብሔር እና የሰይጣን ተጋድሎ አፅንኦት በመስጠት ጽፏል፡፡ እግዚአብሄር በውጊያ ላይ በሚለው መጽሐፍ መግቢያ ላይ በዳን. 10 ጥቂት ትንታኔዎችን ከሰጠ በኋላ ቦይድ እንዲህ ጽፏል፡፡ “መጽሀፍ ቅዱስ ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ መጨረሻው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል መንፈሳዊ ፍጥረታት ስለመኖራቸው ይናገራ፡፡ የነርሱ መኖርም በሰብዓዊ ዘር ላይ በመልካምም ሆነ በክፉ ጎን ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ይህ ፅንሰሐሳብ መጽሀፍ ቅዱስ ስለም በሚናገረው ኃሳብ ውስጥ ማዕከል ነው ብዬ በዚህ ፅሁፍ እሚገታለሁ፡፡”

## የመወያያ ጥያቄዎች:

1. ሌሎች ጥቅሶች ስለ ሰይጣንና ስለ አጋንንት ሀይል ምን ይላሉ? ይህ የሰብአዊነት አሉታዊጎን ነው ተብሎ ብቻ ቢተረጎምና ቢታለፍ ምን የሚረሳ ነገር ይኖር ይሆን?

2. ኒኮሎ ማቺአቬሊ፤ በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ይኖር የነበረ የፍሎረንቲን ጸሀፊ እንዳለው ገዥ በሚገዛው ሰው ከሚወደድ ይልቅ ቢፈራ ይሻላል፡፡ በተቃራኒው ኤለን ጂ. ኋይት ስትጽፍ በሰማይ ሊኖር ኋይት ስትጽፍ በሰማይ ሊኖር እንደማይገባው ሲወሰንበት እንኳን የጥበብ ሁሉ ምንጭ የሆነው አምላክ ሰይጣንን አላጠፋውም፡፡ የፍቅር አገልግሎት ብቻ በርሱ ዘንድ ተቀባይነት ስላለው፤ የፍጥረታቱ ታማኝነትም በእርሱ ፍትህና ቅንነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ሳይጣን ወዲያው ቢጠፋ ኖሮ የሰማይ ፍጥረታት እና የሌላ አለም ነዋሪዎች በሙሉ የሀጢያትን ባህሪና ያመጣብንን ቅጣት የእግዚአብሔርንም ምህረትና ፍትህ ለማየት አይችሉም ነበር፡፡ ወዲያውኑ ቢያጠፋው ኖሮ እነርሱ ከፍቅር በመነጨ ሳይሆን በፍርሃት እግዚአብሄርን ያገለግሉ ነበር›› The Great controversy, pp.498- The Great controversy, pp.498-499 እግዚአብሔር ለምንድ ነው በፍርሃት ሳይሆን በፍቅር እንድናገለግለው የሚፈልገው?